# *ክፍት ደብዳቤ ለፕረዚዳንት ኢሳያስ ኣፈወርቂ !*

# ኢትዮጵያውነት የኤርትራን ሕዝብ በማቆርቆዝ ኣይረጋገጥም ! እንኳንስ የኤርትራ ሕዝብ ቅማልም ቢሆን ሱሪ ያስፈታል !

---

**ከኢትዮጵያዊ ወታደር፡፡**

**የኢትዮጵያ ወታደር ሁኜ ኤርትራ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ትግርኛ ብማርም ፡ ጽሑፍ ላይ ሲሆን ግን እጅግም ስላልሆንኩኝ ፡ እርስዎ ደግሞ በበኩልዎ ፡ ኣማርኛን በደምብ የሚያቀላጥፉ እንደመሆንዎ መጠን ፡ መልእክቴን በኣማርኛ ሳስተላልፍ ከይቅርታ ጋር ነው።**

**የኢትዮጲያና የኤርትራ ሕዝብ ወንድማማችነት እንዲሁም ኣንድነት፡ ከዛም ኣልፎ ኣብሮ የመኖር ባህልና ዘላቂነትን፡ ከሩቅ ኣስተውለው ለ50 ዓመታት ሙሉ ሳይሰለቹ፡ ትዕግስትና ረቂቅነት በተሞላበት የሰለጠነ ምስጥራዊ መዋቅር በመዘርጋት ፡** *የኛ ሰው በሳህል* **፡ ሆኖው ሌትና ቀን በመስራት፡ የኤርትራና የኢትዮጵያ ዳግም ውህደት እግቡ ላይ ኣድርሰውታል፡፡**

**ይህ ወደር የለሌው ተልእኮ ወይንም ሚሽን ከግቡ በማድረስዎ ፡ ተኣምር ድንቅ ጭራሽ የማይታሰብ ሚና፡ እደመሆኑ መጠን በኔ በኩል** *„ የኛ ሰው በሳህል ፡ የዘመኑ ታላቅ ኢትዮጵያዊ „* **የሚለውን ስያሜ ሰጥቸዋለሁኝ። 50 ዓመታት ሙሉ ያካሄዱት ምስጢራዊ ሚሽን ፡ በዓለም ውስጥ እስከዛሬ ድረስ ከታዩት ታላላቅ ሰላዮች ፡ እንደነ ጎልድበርግ ፡ ክላስውስ ፉኩስ፡ ማታ ሃሪ ፡ የመሳሰሉትን እንኳን ሊወዳደሩት ኣይችሉም።**

**50 ዓመታት ሙሉ የጣሩለትን የኣንድነት ስራ ካገባደዱ ወዲህ፡ ከዶክተር ኣቢይ ጋር ያደረጉትን ስምምነት መሰረት በማድረግ፡ የኣስመራ መስመር ተከፍተዋል የሚል ኣስደሳች ዜና ከሰማሁኝ ወዲህ ለ30 ዓመታት ያህል የናፈቅኩዋትን ኤርትራ ለመጎብኘት በጣም ጓጓሁኝ። ኣላስቻለኝም። የምይዘውና የማደርገው ጠፋብኝ። የናት ጡት ለመጥባት እንደሚጣደፍ ህጻን ሁሉ፡ መቆየት ኣልቻልኩም። ወዲያው የኣውሮፕላንን ትኬት ኣስቆርጬ ከኣንድ ሳምንት በህዋላ ኣስመራ ኤርፖርት ገባሁኝ።**

**ኣስመራ እንደደረስኩኝ፡ የቀድሞ ጓዶኞቼን ኣስቀድሜ ነግሬኣቸው ስለነበር ፡ ኤርፖርት ላይ ተቀበሉኝ እና ሁላችንም ተቃቅፈን እንባ እያፈሰስን ናፍቆታችን ካወጣን ወዲህ፡ ይዘውኝ ኤርፖርት ኣጠገብ ከሚገኘው ኣስመራ ፓላስ ሆተል ወሰዱኝ። ሆቴል ውስጥ ቁጭ ብለን፡ የዱሮውን ኣንስተን ከተጫወትን በህ መሸትሸት ከማለቱ በፊት „ እስቲ ከተማውን እንየው !!! እንደ ሙሽሪት እኮ እዚህ ወተፋችሁኝ !!! በማለት ከተማይቱን ለማየት ጓጓሁኝ።**

**የተሰጠኝ መልስ ግን ጭራሽ ያልጠበቁት ነበር ፡፡ ኣንደኛው ጓደኛየ ጸጉሩን እያከከ ኣንገቱን ኣቀርቅሮ** *„መሄዱንማ ኣንሄደዋለን„* **ብሎ ዝም ኣለ፡፡ ሁለቱም ዝም ኣሉ፡፡ እኔም በልቤ ምን የተደበቀ ነገር ኣለና ነው ኣልኩኝ፡፡ ፈራሁኝ፡፡ ኣዲስ ሃሳብ ጭንቅላቴን መታው፡፡ እንደ ዱሮ ህዝቡ ፡ በየመንገዱ ‚ኪድ ኣድጊ‚ እያለ ይሰድበኝ ይሆን ! ጥላቻው ኣላለቀም እንዴ! ማለት ጀመርኩኝ፡፡**

**ከትንሽ ዝምታ በህዋላ ኣንዱ ጓደኛየ ፡** *„ ከተማውን ምን ታይበታለህ ! ኣስመራ እንደዱሮ እንዳይመስልህ ! መሄዱንማ እንሄደዋለን ! ለማንኛውም ኣትደንግጥ ! የልብ በሽታ እንዳይይዝህ ! „* **ኣለኝና ፡፡ „ አረ ግድ የለም„ ብዬ ተያይዘን በመኪና ሄድን።**

ከግማሽ ሰዓት በማያልፍ ግዜ ፡ እምባሶይራ ሆቴል ኣከባቢ ደርሰን እዛው ኣከባቢ መኪናችንን ኣቆምናት፡፡ ከዛ፡ በእግራችን መንገዱን ተያያዝነውና፡ ባር ቶሪኖን ኣልፈን ወደ ሞኖፖል በውረድ፡ ኣባ ሓበሽ ፐላሶ በመድረስ ፡ ቀጥሎም በእንዳ ማርያም በኩል ሸቅብ በመውጣት ፡ በስተግራ በመታጠፍ ኢትዮጵያ ኣደባባይ ( ያሁኑ ሜዳ ኤርትራ ) ከደረስን በህዋላ ፡ እንዳ ካንዘን ኣልፈን ፡ ካተድራል ደረስን፡፡ በመጨረሻም ፡ትንሽ ለመቅመስና ላማሳረፍ ብለን ካምቦሽታቶ ከሚገኘው ኣንድ ካፈተርያ ቁጭ ኣልን።

ያየሁት ሁሉ ኣሳዛኝ ጉድ ነው ፡፡ ገና ለገና ከመኪና ኣንደወረድኩኝ 10 ሜተር ሳልርቅ መንገዱ ተቆፋፍሮ ፡ ኣደናቅፎኝ ወድቄ ጥርሴ ወላልቆ ነበር። ማርቻፔዲው ተላልጦ ኣሸዋ ፡ ኣፈርና “ ኮረኮንች እንዲሁም የጋሪ ፋንድያ ተደባልቆዋል። ቤቶቹ ግድግዳቸው ተላልጦ ፡ ቶኖኮውና ድንጋዩ፡ እላይህ ላይ እንዳይወድቅ ከግንቡ ራቅ ብለህ ነው የምትጓዘው። በየመንገዱ የተተከሉ ዘንባባዎች ዞር ብሎ የሚያያቸው ስለሌለ ቅርጫፋቸው ወደታች ተንጠልጥሎ ጸጉርህንና ፊትህን ኣንደ ማረሻ ይጭረዋል። የቤቶች መስተዋት ኣልፎ ኣልፎ ተሰባብሮ ነፋሱ ያፋጫል። የለማኙ ብዛት ኣይጣል ነው። ለማኞች ኣንደ ጅብ ግራና ቀኝ ይከቡሃል። „ ራብኝ ! ኣባቴ ድንበር እየጠበቀ ነው ! ሰልዲ ሃበኒ ! ፡ የሚሉ ህጻናትና እናቶች መንገድ ኣያሳልፉም። ራሴን ማመን ኣቃተኝ። ለመሆኑ ኣስመራ ነው ወይ ያለሁት ኣልኩኝ። መቀሌ ከተማ በሃይለስልሴ ዘመን ኣስታወሰኝ።

ደህና ልብስ የለበሰ ፡ የሚስቅና ደስተኛ ሰው ከተማ ውስጥ ኣይታይም ፡፡ ሁሉም ኣንገቱን ኣቀርቅሮ የሚሄድ ሃዘንተኛ ነው። ያ ዱሮ ጣልያንኛ እየደባለቀ .. ቻው ፒኮሎ „እያለ ከሩቁ እየተጣራራ በመሄድ፡ እየሳቀ ሙቀትና ደስታ የሚሰጥ ተናፋቂ ድምጽ ዛሬ የለም። ኣስመራ የምትሃት ከተማ ትመስላለች። ከተማይቱ ከ 15 ኣስከ 50 መካከል ፡ ዕድሜ ያለው ወንድ ኣይታይባትም። ህጻን ወይም ሴት ወይንም ሽማግሌ ብቻ ነው የምንቀሳቀሰው። በየቦታው የተጣለው የኣንጥንትና የኣሮጌ ቆዳ ፡ ግማቱ ኣገርያስለቅቃል። የዱሮ ቄራ ይመስላል። ቁጭ ያልንበት ቡና ቤት እንኳን ቢሆን፡ የቡናው ብርጭቆ ፡ በባልዲ ውሃ ነው የሚታጠበው። የውሃ ቡዋንባው ኣይሰራም፡፡ ዘገነነኝ ኣሳዘነኝ ፡፡ ሽንት ቤት ገብቼ ኣንባየን ለቀቅኩትና ተመልሼ ጓዶኛቼ ጋ ቁጭ ኣልኩኝ።

የኔ ሁናቴ በማየት ነው መሰለኝ ጓደኞቼ ፡ „ ሕጂከ ርኢካየዶ „ ኣሉኝ ፡፡ ምንም ኣልተናገርኩም ፡፡ ራሴን በማንቀሳቀስ ኣዎን ከማለት ባስተቀር። ያን ሁሉ ትዕዝብት ካስተዋልኩኝ በውሃላ ኣንድ ነገር ትዝ ኣለኝ ፡፡ ጭንቅላቴን መታው። የኣልኣሚን ኣብደለጢፍ ዘፈን „ ደሓን ኩኒ ኣባሻውል !!!!! ዓባይ ኣባሻውል ከይፈረሰት ከላ ......!!!! የሚለው። ባጭሩ ባሁኑ ጊዜ ያቺ የዱሮ ኣስመራ ፡ „ ከኣስመራ ጻዕዳ ወደ ኣስመራ ገሃነም „ ተቀይራለች።

ክቡር ፕረዚደንት

ኢትዮጵያዊነት የኤርትራን ህዝብ እንደጠላት ወስደህ በማሰቃየትና ፡ ድህነት ውስጥ በመክተት ኣይረጋገጥም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ኣብሮ ለማደግና ለመደማመር ካልሆነ ፡ ኣንደኛው ብሔረ ሰብ ፡ ሌላኛውን ሕብረተሰብ በማጉደልና በማደህየት እኩልነት ኣይሻም። እንደማይሳካም ያውቃል፡፡ ካለፈው ታሪክ ተምረዋል። የኤርትራን ሕዝብ የማደህየት ስትራተጂ ለጃንሆይም ኣልጠቀመም። እንዲያውም ኣንደ ጎርፍ ጠራረጋቸው እንጂ።

ኡነቱን ላውጣው ይፈቀድልኝ፡፡ ብፈረንጅ 1970 ገደማ ፡ እንደሚያስታውሱት እርስዎ ከኣሜሪካው ኮነሬል ሮላንድ ካፐላንና ፡ እንዲሁም ከእስራላዊው በደቀምሓሬ የኮማንዶ ኣሰልጣኝ ከነበረው ለቪ የተባለው ፡ ለእርስዎ የተሰጠ ምሽን ወይም ተልኮ ፡ „ *የኣረቦች በቀይ ባህር የመስፋፋት ኣደጋ ለመግታትና በዝያን ጊዜ የነበረው የኮምኒስት የመስፋፋት ዕቅድ በረጅሙ ለምቅጨት „* ኣንጂ የኤርትራን ሕዝብ ኣንደ ጠላት ኣይተህ በድህነት በስደት እና በድንቁርናና ለማማቀቅ ኣልነበረም። እርስዎ የተሰጠዎትን ማንዴት ጥሰውታል ። የርስዎ ምሕረተ ቢስ ኣሰራር ፡ ሌላው ቀርቶ በሰው ልጅ ውለታ ቢታይ እንኳን ይዘገንናል፡፡ የኤርትራ ሕዝብ ፡ለርስዎና ከመሃል ኣገር ወደ ኤርትራ ለመጡ

**ወላጆቻችዎ፡ „ ወዲ ላምና„ እያለ አቅፎና አከናንቦ አስከ መሪነት ድረስ ያደረሰ ስመጥሩ ህዝብ ነው። በዓይነ ቁራኛ የሚያዩበት ኢሰብአዊ ተግባር ላዩ ላይ የሚፈጽሙበት ምክንያት የለም፡፡ ካንዳንዱ ሞኝ ኢትዮጵያዊ የሚሰጠው „በለው ! አለሁልህ !„ የሚለውን ቃል ባይሰሙ ጥሩ ነው፡፡ በአሁኑ ግዜ ዶላር ተከፍሎት በየጠጅቤቱ** *„ ኣንተ ነህ ፡ ኣንተነህ፡ ታማኝ ወታደር ! ከኣስመራ ተነስቶ ኣዋሳ ሚያድር !! ተገንጣዩን ሁሉ የሚያሽቀነጥር„* **እያለ የሚያራግበውን ወስላታ ኣዝማሪ ሰምተው ባይተኙ ጥሩ ነው ።**

ክቡር ፕዚዳንት

**የዘነጉት ኣንድ ጉዳይ ኣለ የኤርትራ ሕዝብ ትዕግስተኛ እንጂ ፈሪ ኣይደለም፡፡ የተነገርው ሁሉ ኡነት ወስዶ የሚያምን ፡ ኣማኝ ፡ መንፈሳዊ፡ ህዝብ ነው እንጂ ደንቆሮ ኣይደለም፡፡ እርግጥ የፖሊካ ኣሻጥርና ትሪክ የሚጎድለው፡ „ የኔ መብት ምንድንው „ የሚል ጥያቄ የማያነሳ የዋህ እንጂ፡ ቦምብና ታንክ የሚፈራ ህዝብ ኣይደለም። እስከ ዛሬ ድረስ እርስዎ ላይ ያሳየው ትዕግስት** ***<u>እርሰዎ ፡ የኛ ሰው በሳህል መኖርዎን</u>*** **ስላላወቀ ብቻ ነው። የዱባለ ታላቅ ወንድም እንደሆኑ፡ ኣሁን ነው ቀስ በቀስ የበራለት።**

**ሕዝቡ እስከ ዛሬ ያሳየው ትዕግስት „ ልጆቻችን ነጻነት ኣመጡልን !! ጊዜ እንስጣቸው !! ኣሳልፈን ኣንስጥ !! „ ከሚል ኣስተዋይ ልቦና የተነሳ ኣስተሳሰብ ነው። ኣሁን ግን ሁሉም ነገር ግልጽ ሆኖ በርተዋል። እርስዎ በኣሜሪካዊው ሮናልድ ካፕላንና በኢሳራኤላዊው ሊቪ በኤርትራዊ ትግል ውስጥ የተወሸቁ ኤጀንት ኣንደነበሩ ምስጢሩ ፈነዳ፡፡ ግልጽ ሆነዋል። ኣቶ ብርሃነ ኣብርሃ ፡ ኣቶ መስፍን ሓጎስ ፡ ኣቶ ተስፋሚካኤል ጀርጆ ፡ ኣቶ የማነ ተክለጊዮርጊስ ፡ የሰጡት ማብራርያ ራሱ በቂ መረጃ ነው። የኤርትራ ሕዝብ ደሙ ፈልተዋል ፡፡ ኣንዴ ከቀረጠ ኣይመለስም። እንደሚያውቁት ይህ ሕዝብ ባለፈው 500 ዓመት የወታደርነትና የቆራጥነት ታሪክ ያሳለፈ ሕዝብ ነው፡፡ ያለ ምንም ማጋነን፡ ባለፉት ኣምስት መቶ ( 500 ) ዓመታት ሙሉ በገባበት ጦርነት ፡ ተሸንፎ ኣያውቅም። ከቱርኮች ጎን ተሰልፎ ኣሸነፈ ፡፡ ከጣልያኖች ጎን ተሰልፎ ኣሸነፈ ፡፡ ከእንግሊዞች ጎን ተሰልፎ እሸነፈ ፡፡ ለነጻነት ተሰልፎ በኣፍሪካ ተወዳዳሪ ያልነበረውን የደርግን ሰራዊት ገረሰሰ ። ሌላው ቀርቶ በፈረንጅ ኣቆጣጠር 1976 ፡ ፡ እስከ 100,000 የሚያክልውን ፡„ የደርግ የዘማች ወታደር ፡ ራዛ ፕሮጀክት ተብሎ አርትራን ለምውረር ብትግራይ ድንበር ፡ የተሰባሰበ ፡ የሸመጃና ሕዝብ ብቻውን ያለ ምንም የታጋይ እርዳታ፡ በኣራት ቀን ውስጥ ብትንትኑን ኣወጣው፡፡ ሌላው ቀርቶ በኣሁኑ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ፡ ዓሰብን ለመያዝ በተደረገው ትንንቅ፡ እርስዎ ከሀርማን ኮሀን ጋር ተስማምተው፡ የኤርትራን ሰራዊት ዓሰብን ለቆ ፡ወደ ምጽዋ እንዲያሽገሽግ፡ የሰጡትን ትእዛዝ „ኣልቀበልም ! „ ብሎ፡ በጀግንነት ተዋድቆ ፡ ኣገሩን ያዳነ ፡ ወደር የሌለው ቆራጥ ሕዝብ ነው። ከላይ እንደገለጽኩት ፡ እስከ ዛሬ ድረስ ሕዝቡ ፡ እርስዎ ላይ ያሳየው ትዕግስት** ***<u>እርሰዎ ፡ የኛ ሰው በሳህል መኖርዎን</u>*** **ስላላወቀ ብቻ ነው።**

ክቡር ፕረዚዳንት

**በመጨረሻ፡ ኣንደ ኢትዮጵያዊ ወንድምዎ መጠን የምሰጥዎት ምክር ካለ፡ የያዙትን ስትራተጂ ጠቅላላ በመቀየር ፡ የአርትራን ሕዝብ በሰላም ካልመሩ ፡ እስረኞችን ካልፈቱ ፡ ሕገ መንግስቱን በተግባር ካላቅዋቃሙ ፡ <u>የእርስዎና የልጆችዎ ዕድሜ ባጭሩ ኣንደሚቀጭ ይወቁ። ኣንኳንስ የኤርትራ ሕዝብ ቅማልም ቢሆን ሱሪ ያስፈታል።</u>**

ከኢትዮጵያዊ ወታደር፡፡

---

***በታጋዩ ኢሳያስ ኣፈወርቅና በ ሲ ኣይ አ መካከል የተደረገው የዚያን ግዜ ምስጢራዊ ግንኙነት ፡ የችግኝ ተክል seed planting በሚል ኮድ የሚጠራ ፡ በፕሮቶኮል ቁ. 21/9/62 1038 / 1039/18/31 ሀ1/19/ሰ/2 ተመዝግበዋል ። ሲድ ፕላንቲንግ የተባለበት ምክንያት ፡ በዚያን ግዜ ኮሎነል ካፕላንድ፡ ለከሸር ኣፕ እንዲመቸው በማለት ፡ ማይ ሓባር ውስጥ ፡ የልማት ችግኝ ስለጀመረ ነው፡፡**